# ጎጃም “በትረጽድቅ” ስኮላርሺፕ
# አራተኛው ዓመት

ዶ/ር አብርሃም በቀለ

የበትረጽድቅ ስኮላርሺፕ ተግባር ላይ በዋለበት አራተኛው የትምህርት ዘመን አመርቂ ውጤቶችን በተለያዩ ዘርፎች አስመዝግቧል። ከሁሉ አስቀድመን ፕሮግራሙን ለዚህ ላበቁት ልግስናቸው ላልተቋረጠብን ደጋፊዎች፣ ጉልበታቸውንና እውቀታችውን ለዳረጉን የፕሮግራሙ መሪዎችና አስተባባሪዎች ምስጋናችንን፣ አድንቆታችንንና፣ አክብሮታችንን እንገልጻለን። ችርነቱ ላልተለዬን አሞላክም፣ ምስጋና ይድረሰው።

| የስኮላርሺፕ አሸናፊዎች ቁጥር | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2001 | | | 1998-2000 | | | አጠቃላይ | | |
| ዞን | ሴ | ወ | ድምር | ሴ | ወ | ድምር | ሴ | ወ | ድምር |
| አዊ | 5 | 12 | 17 | 14 | 42 | 56 | 19 | 54 | 73 |
| ምዕራብ | 8 | 22 | 30 | 23 | 67 | 90 | 31 | 89 | 120 |
| ምሥራቅ | 13 | 30 | 43 | 31 | 87 | 118 | 44 | 117 | 161 |
| ባሕር ዳር | 3 | 7 | 10 | 9 | 24 | 33 | 12 | 31 | 43 |
| ድምር | 29 | 71 | 100 | 77 | 220 | 297 | 106 | 291 | 397 |

በ 2001 የትምህርት ዘመን ከ 27 ት/ቤቶች ለተመረጡ 100 የ11 ኛ ክፍል ጎበዝ ግን ችግረኛ ለሆኑ ተማሪዎች ዕርዳታ ተሰጥቷል። ይኸውም ዘንድሮ ወደ 12ኛ ክፍል የተዛወሩትን 97 ያለፈው ዓመት ተመራጮች ጨምሮ የዚህን ዓመት ተጠቃሚዎች ቁጥር 197 ያደርጋል። ስኮላርሺፑ ከተጀመረ 1998 የትምህርት ዘመን እስከዛሬ ጠቅላላ ተጠቃሚ የሆኑት ተማሪዎች ቁጥር 397 ደርሷል። ለአንድ ተማሪ የሚሰጠው ስኮላርሺፕ ለሁለት ዓመት ስለሆነም እስከዛሬ የተሰጠው ዓመታዊ ስኮላርሺፕ ቁጥር 644 ደርሷል።

| የስኮላሺፕ ድጋፍ ያገኙ ተማሪዎች ቁጥር | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የትምህርት ዘመን | ክፍል | | ጠቅላላ ያመቱ ተጠቃሚዎች ድምር | አዲስ ተመራጮች (እድገት = increment) |
| | 11 | 12 | | |
| 1998 | 53 | 47 | 100 | 100 |
| 1999 | 100 | 50 | 150 | 100 |
| 2000 | 97 | 100 | 197 | 97 |
| 2001 | 100 | 97 | 197 | 100 |
| ድምር | 350 | 294 | 644 | 397 |

## የሴቶች ጉዳይ

ከጥንስሱ ይህ ስኮላርሺፕ የሴት ተማሪዎችን ችግር በማጤን፣ ሴቶችን ለማስተማር የሚደረጉ ጥረቶች በታሪክ ያስገኙትን ውጤቶች ግንዛቤ በመውሰድ፣ ተወዳድረው ከሚያሸንፉት በተጨማሪ ለሴቶች 25 ከ100 ቦታዎች እንዲመደቡላቸው ደነገግን። በዚያው መሰረት እስከዛሬ ተጠቃሚ ከሆኑት 397 ተማሪዎች 106 ወይም 27% ሴቶች ናቸው። የሴት ተማሪዎቻችን ጉዳይ በያጋጣሚው እየተደጋገም ስለሚነሳ ቁጥራቸውን ለማሳደግ የሚቻልበትን ብልሃት ለመቀየስ ከፕሮግራሙ አስተባባሪዎችና ደጋፊዎች ጋር ውይይት አካሂደን ስምምነት አድርገናል። መጠነኛ ዝርዝር ታች “የታቀዱ ጉዳዮች” ክፍል ውስጥ ይገኛል።

## ውጤት

በትረጽድቅ ስኮላርሺፕ 198 ተማሪዎችን (47 በ1998 53 በ1999 እና 98 በ2000 ዓም) አስመርቆ ለዩኒቨርሲቲ የከፍተኛ ትምህርት አብቅቷል። የዚህ ስኮላርሺፕ ዓቢይ ዓላማ የጎበዝ ተማሪዎችን የኢኮኖሚ ችግር በመቅረፍ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ የጎጃም ተወላጆችን ቁጥር ማበርከት ስለሆነ በዚህ ረገድ አመርቂ ውጤት አስገኝቷል። ተማሪዎች የተመደቡባቸው የጥናት መስኮችም ውጤቱን በተጨማሪ ይበልጥ አርኪ አድርገውታል። ከ 1998 - 2000 ወደ ዩኒቨርሲቲ

| ከ1998 - 2000 ዩኒቨርሲቲ የገቡ ተማሪዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የተመደቡባቸው የትምህርት መስኮች | 1998 & 1999 | 2000 | ድምር | % |
| የሕክምና ጤና ሳይንስ | 70 | 66 | 136 | 69 |
| ምህንድስና | 16 | 4 | 20 | 10 |
| ሕግ፥ ቢዝነስ፥ ኢኮኖሚክስ | 4 | 1 | 5 | 2 |
| ሌሎች መስኮች | 2 | 25 | 27 | 14 |
| ምድባቸውን ያላሳወቁ | 7 | 2 | 9 | 5 |
| ፈተና ያልወሰዱ | 1 | | 1 | |
| | 100 | 98 | 198 | 100 |

ከገቡት 198 ወጣቶች 69% በሕክምናና ጤና ሳይንስ ሲሰማሩ 10% በምህንድስና ሳይንስ ተመድበዋል ሌሎች መስኮች ባልናቸው ውስጥ ካሉት 14% አብዛኞቹ የሚከታተሉት ሳይንስ-ነክ ትምህርቶችን ነው። ባላፉት ሪፖርቶቻችን እንደገለጽነው እነዚህ የሳይንስ መስኮች ከፍተኛ ውድድር ያለባቸው በመሆኑ ተፈላጊውን ውጤት በማግኘት ተማሪዎቻችን ለዚህ ዕድል ስለበቁልን በድጋሚ እጅግ ተደስተናል፣ ኮርተናልም።

እጅግ አኩሪ ከሆኑት የስኮላርሺፑ ውጤቶች ላብነት



ያህል ሁለት እንጠቅሳለን። በ1998 ዓም ባቀረብነው ሪፖርት ይስተዋወቅናት ተማሪ ማሪቱ ካሤ መኮንን (ከዳንግላ)፥ እንዲህ ብላን ነበር፤

"... የበትረጽድቅ ስኮላርሽፕ ባይደርሰኝ ትምህርቴን ማቋረጥ እገደድ ነበር .... "

ማሪቱ በጂማ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ፋኩልቲ ዘንድሮ ሁለተኛ ዓመቷን ታጠናቅቃለች።

በ1999 ሪፖርታችን ያስተዋወቅናት ተማሪ ፍቅርአዲስ ካሤ ብርሃኑ (ከቋሪት ወረዳ) ደግሞ እንዲህ ብላን ነበር፤



"…. ወላጆቼ የሚኖሩት ገጠር ነው። አባቴ ሥራ ፍለጋ ከተሰደደ ቆይቷል፡ የት እንደደረሰ አናውቅም። እናቴ እዚያው አለችበት ገጠር ተቀጣሪ የቤት ሠራተኛ ነች፡ እኔን ለመርዳት ይቅርና ራሷንም ማስተዳደር አትችል። ..... እስከ ፲ኛ ክፍል ለመማር የቻልሁት ካንድ ጠላ እየሸጠች ከምትኖር ድሃ ዘመዴ ተጠግቼ ነበር፡ ከትምህርት ቤት በኋላ ዘመዴን በጉልበት ሥራ እረዳታለሁ፡ ለጥናት ገዜ ያጥረኝ ነበር፡ .... እንደምንም ብዬ 3.28 አገኘሁ፡ የማጥኛ ጊዜ እንደልቤ ቢኖረኝ 4.00 አገኝ ነበር። .... ዛሬ ይህን ስኮላርሺፕ ስላገኘሁ እንደልቤ አጠናለሁ፡ ዕድሌ እንደድሮው ጨለማ አይደለም፡ ከእግዚአበሔር በታች የማመሰግነው ይህን ስኮላርሺፕ ያመቻቹትን ነው። .... ዋጋችሁን እግዚአብሔር ይክፈላችሁ። ... ለሌሎች የኔ ቢጤ ችግረኞችም እንድትደርሱላቸው አደራ እላለሁ።..."

| ተመራቂዎች የተመደቡበት ቦታዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 1998 & 1999 | 2000 | ድምር | % |
| ጎንደር | 15 | 16 | 31 | 16 |
| ጂማ | 15 | 4 | 19 | 9 |
| ባሕር ዳር | 14 | 5 | 19 | 9 |
| አዋሳ | 11 | 13 | 24 | 12 |
| መቀሌ | 11 | 4 | 15 | 8 |
| አዲስ አባባ | 9 | 10 | 19 | 10 |
| ሐረማያ (የድሮው አለማያ) | 6 | 4 | 10 | 5 |
| አርባ ምንጭ | 3 | 1 | 4 | 2 |
| አዳማ | | 30 | 30 | 15 |
| ደብረ ማርቆስ | | 7 | 7 | 4 |
| ሌሎች ቦታዎች | 8 | 3 | 11 | 6 |
| ፈተና ያልውሰዱ | 1 | | 1 | |
| ምድባቸውን ያላሳወቁ | 7 | 1 | 8 | 4 |
| ድምር | 100 | 98 | 198 | 100 |

ፍቅርአዲስ በሃረማያ ዩኒቨርሲቲ (የድሮው አለማያ) የጤና ሳይንስ ፋኩልቲ ዘንድሮ የመጀመሪያ ዓመቷን አጠናቀቀች።

## የድርጅት ጉዳዮች

ባለፈው ዓመት እንዳነሳነው ጎሽና ካናዳ DevXchange International ከሚባል ካናዳዊ ግብረ-ሠናይ ድርጅት ጋር በመተባበር ለስኮላርሺፑ ዕርዳት ከግብር ነፃ በሆነ መንገድ ማሰባሰብና ወደ በትረጽድቅ ስኮላርሺፕ-ኢትዮጵያ ማስተላለፍ በዚህ ዓመት ጀመረ።

በተጨማሪም ክዚሁ ድርጅት ጋር በመተባበር ጎሽና ካናዳ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችና ለኮሌጆች የሚሆኑ መጽሐፍቶችን አሰባስቦ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ አመርቂ ግሥጋሴን ያሳየ ዝግጅት አድርጓል።[1]

በኢትዮጵያ ያለው የበትረጽድቅ ካሣ ስኮላርሺፕ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጠቅላላው 9 አባላት ያሏቸው ሦስት ንዑስ ኮሚቴዎች (1) የውጭ ግንኙነት (2) የሀገር ውስጥ ግንኙነት እና (3) አስተዳደርና ፋይናንስን የሚመለከቱ ሰይሟል። የኮሚቴዎቹ አባላት በተለያዩ የመንግሥት፣ የዓለም አቀፍና፣ የግል ድርጅቶች በከፍተኛ ደርጃ የሃላፊነት ቦታዎች ያገለገሉ አንጋፋ ባለሙያዎች ናቸው።

ሁለት የሰሜን አሜሪካ ኮሚቴ አባሎች፥ አቶ ተሰማ ቢተው በ1999 የትምህርት ዘመንና እና አቶ አለባቸው በቀለ በ2001 የትምህርት ዘመን ለእረፍት ኢትዮጵያ በነበሩበት ወቅት ከበትረድድቅ ካሣ ስኮላርሺፕ ኮሚቴ አባላት ጋር ተገናኝተው ሰፋ ያሉ ውይይቶችን አካሂደዋል። አቶ አክሊሉ አፈወርቅ፣ የውጭ ግንኙነት ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ፥ አሜሪካ በእረፍት ላይ እያሉ የሰሜን አሜሪካን ኮሚቴ አባላት በቴሌ`ኮንፈረንስ ለሁለት ሰዓት ያህል አወያይተዋል። እንዲሁም አቶ አዲስ አንተነህ የበትረጽድቅ ካሣ ስኮላሺፕ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ በመስከረም ወር ሰሜን አሜሪካ ለእረፍት በነበሩበት ወቅት የሰሜን አሜሪካውን ኮሚቴ በቴሌኮንፈረንስ ለሁለት ሰዓት ያህል አነጋግረዋል። ወደ ካናዳም ተጉዘው በዚያ ከሚገኘው የጎጃም ልማት ማህበር አባላት ጋር ውይይት አድርገዋል።

ሚ/ር ቦብ ብላክ (Bob Black)፥ ከጎሽና ካናዳ ጋር የተሻረከው ግብረ-ሰናይ ድርጅት DevXchange ቦርድ አባል ለሥራ ኢትዮጵያ በነበሩበት ወቅት የበትረጽድቅ ካሣ ስኮላርxiፕ ኮሚቴ አመራሮችን አነጋግረዋል። በጎጃም ልማት ማሕበርና በኮሚቴውም ሥራዎች መደሰታቸውንም ገልጸዋል።[2]

## የገንዘብ ዕርዳታ አሰባሰብና ስርጭት

### በዩናይትድ ስቴትስ (USA)

ዘንድሮ በዩናይትድ ስቴትስ $10,000 ተሰባስቧል። ይኸውም ካለፉት ሁለት ዓመታት የተሻለ ውጤት ነው። ከዚህ ውስጥ $3,000 ከሎስ አንጀለስ አካባቢ፣ $5,650 ከዲሲ አካባቢ፣ $750 ከሺካጎ አካባቢ ተገኝቷል። በዚሁ የትምህርት ዘመን $7,500 ወደ ኢትዮጵያ ተላልፏል።

በዚህ ዓመት ካለፉት ለየት ያለ ዕርዳታ ደርሶናል። በዲሲ-ሜትሮ አካባቢ የሚኖሩ ባልና ሚስት፥ አቶ <u>መሰረት ተሰፋየ</u> እና ወ/ሮ ቆንጂት ምህረቴ፥ መሥሪያ

1 ዝርዝሩን ተያይዞ በቀረበውን GDA - Canada LIFE Scholarship Report ይመልከቱ።

2 እንደላይኛው

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከዩናይትድ ስቴትስ ዷሪዎች የተገኘ የገንዘብ ዕርዳታ (2001) | | | |
| ከሎስ አንጀልስ አካባቢ የተሰበሰበ | | | |
| | ጎሻና ኤል ኤ | 2250 | |
| | አቶ ስለሺ ደረጀ | 300 | |
| | ወ/ት ሰላም ወ ፈንቴ | 150 | |
| | ወ/ት ገሊላ ወ ፈንቴ | 150 | |
| | ወ/ት ሃና ደበላ | 150 | |
| | | | $3,000 |
| ከዲሲ-ሜትሮ አካባቢ የተሰበሰበ | | | |
| ከባሕርዳር የቤተሰብ ማሕበር አባላት | | | |
| | ባሕርዳር የቤተሰብ ማሕበር | 2250 | |
| | ወ/ት ወይንሸት ያረጋል | 150 | |
| | አቶ አለባቸው በቀለ | 150 | |
| | አቶ አምሳሉ በቀለ | 150 | |
| | ዶ/ር አብርሃም በቀለ | 150 | |
| | | | $2,850 |
| ከዲሲ-ሜትሮ አካባቢ ዷሪዎች የተሰበሰበ | | | |
| | ወ/ሮ ቀንጇት ምሕረት | 500 | |
| | አቶ መሰረት ተስፋየ | 500 | |
| | ሲስተር ጥሩአይነት አበበ እና አቶ ተፈሪ መኮነን | 450 | |
| | አቶ ታደለ ጃኔ የኔጌታ | 450 | |
| | ሚ/ር ና ሚ/ስስ አለን ቶማስ | 150 | |
| | አቶ ይግዛው መንበሩ | 150 | |
| | አቶ ጥላሁን ደረሰ | 150 | |
| | አቶ ለማ አትክልቴ | 150 | |
| | አቶ ሙሴ መንግስቴ | 150 | |
| | አት መኩሪያው ተረፈ | 150 | |
| | | | $2,800 |
| ከሺካጎ አካባቢ የተሰበሰበ | | | |
| | አቶ ሙሉቀን ጥላሁን | 150 | |
| | አቶ አያሌው ካሳ | 150 | |
| | አቶ ከፋለ ገላው | 150 | |
| | ፕሮፍ ይታይህ ዘላለም | 150 | |
| | አቶ ደሳለኝ ካሣ | 150 | |
| | | | $750 |
| ከሌላ አካባቢዎች | | | |
| | ዶ/ር ባላገር አደመ | 450 | |
| | አቶ ታደለ መኮነን | 150 | |
| | | | $600 |
| | ጠቅላላ ድምር | | $10,000 |

ቤታቸው በሠራተኞቹ ሥም ለበጎ አድራጎት ከሚያደርገው ልግስን የነሱን ድርሻ $1,000 ለስኮላርሺፑ አበርክተዋል።



ወ/ሮ ቀንጇት ምህረቴና አቶ መሰረት ተስፋየ ከልጆቻቸው ጋር

ለአቶ መሰረት፥ ለወ/ሮ ቀንጇት፥ እና ድርጅታችንን ላስተዋወቀቻቸው የኮሚቴችን አባል ወ/ት ወይንሸት ያረጋል ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን።

ከዚህ ቀደም ደጋግመን እንዳነሳነው ከግለሰቦች ማሰባሰብ እጅግ አድካሚና አስቸጋሪ ስለሆነብን በማንኛውም መልክ የተደራጁ የጎጃም ተወላጆች፣ በተለይም የጎሸና አባል ድርጅቶች የጎሸና ኤል-ኤንና የጎሸና ካናዳን ምሳሌነት በመከተል በማሕበር ይለግሱን ዘንድ አሁንም በትህትና እናሳስባለን።

## በካናዳ

ከላይ እንደገለጽነው ጎሸና ካናዳ ከቀረጥ ነፃ በሆነ ሽሪክ ድርጅት አማካኝነት ማሰበሰብና ወደ ኢትዮጵያ ማስተላለፍ ጀምሯል። ዝርዝሩ ተያይዞ በቀረበው የጎሸና ካናዳ ሪፖርት ቀርቧል። ባጭሩ በ2001 የትምህርት ዘመን ጎሸና ካናዳ ከድርጅቶችና ግለሰቦች $8,220 የካናዳ ዶላር አሰባስቦ ለ30 ተማሪዎች ብቃት ያለው $5,000 የካናዳ ዶላር ወደ ኢትዮጵያ አስተላልፏል።[3]

## በኢትዮጵያ

በአገር-ቤት የሚገኘው የፕሮጀክቱ አስፈጻሚ የበትረጽድቅ ካሣ ስኮላርሺፕ ኮሚቴ እንዳመለከተን በዚሁ የትምህርት ዘመን ካገር ውስጥ ኢ..ብር 104,700 ተሰብስቧል። ከዚህ ውስጥ ኢ..ብር 10,000 “የስኮላርሸፑ ደጋፍ ሰጪ ከነበሩት ከሟቹ አቶ መኮንን ከፍአለ ቤተሰብ ለአርባ ዝግጅት የሚያወጡትን ወጪ ለተማሪዎች ስኮላርሺፕ እርዳታ እንዲውል የሰጡት” መሆኑን ተረድተናል። የአቶ መኮንንን ነፍስ ይማርልን፥ ቤተሰቦችንም እግዚአብሔር ያጥናልን። ተጨማሪ ዝርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ተካቷል።

---

3 እንደላይኛው

| በ2001 ዓ.ም. ለበትረጽድቅ ካሣ ስኮላርሺፕ ገቢ የሆነ | |
|---|---|
| የገቢ ምንጭ | በኢ. ብር |
| ከአገር ውስጥ የተሰበሰበ | 104,200.00 |
| ከሰሜን አሜሪካ (ካናዳና ዩናይትድ ስቴትስ) | 123,654.69 |
| ከባንክ ወለድ | 5,811.76 |
| ጠቅላላ ድምር | 233,666.45 |

## የታቀዱ ጉዳዮ`ች

የበትረጽድቅ ካሣ ስኮላርሺፕ ኮሚቴ ከሰሜን አሜሪካው ኮሚቴ ጋር በመመካከር የፕሮግራሙን ተጠቃሚዎች ቁጥር በያመቱ በ50 በማሳደግ በ2005 የትምህርት ዘመን 500 ለማድርስ አቅዷል። የሴቶችንም ድርሻ አሁን ካለው 30% በ2001 ወደ

| | የትምህርት ዘመን | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጾታ | 2002 | 2003 | 2004 | 2005 |
| ወንድ | 150 | 165 | 200 | 250 |
| ሴት | 100 | 135 | 200 | 250 |
| ድምር | 250 | 300 | 400 | 500 |

40% ከዚያም በያመቱ በማሳደግ በ2004 የትምህርት ዘመን 50% ለማድረስ ታስቧል

በድጋሚ የፕሮግራሙን ደጋፊዎች፥ መሪዎችና፥ አስተባባሪዎች፥ እጅግ በጣም እናመሰግናለን። የገንዘብ፥ ጉልበትና፥ እውቀት ልግስናችሁ እስካልተለየንም ድረስ በሚቀጥሉት ዓመታት ቢያንስ ተመሳሳይ ከተቻለም የላቀ ውጤትን ለማበርከት ባገር ቤትና በውጭ የምንገኝ የስኮላርሺፑ አመራር ኮሚቴ አባላት በሙሉልብ ቃል እንገባለን። ጤና ይስጥልን።

---

## GDA – Canada LIFE Scholarship Report

Mr Tessema Bitew

In the academic year 2008/2009 LIFE Scholarship sent Cdn$5000.00(Five thousand Canadian dollars) which was enough to support about 30 students. LIFE Scholarship would like to thank the following individuals for their generous donation for this noble cause (all in Canadian $).

Honda of Canada Mfg.(HCM) on behalf of Tessema Bitew for his contribution to the LIFE Scholarship project Community Service $500 and HCM AC employees $150, Joao & Silvia Margarido (HCM AC associate $150 totaling $800

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| *Russel Green(BC) | 450 | Dr. Haregua Getu | 200 | **Dr. Melaku Desta(UK) | 150 |
| *Jocelyn & Roger Green | 360 | Getachew Yimenu | 200 | **Dr. Jennifer Considine | 150 |
| Tessema Bitew | 540 | Fasika Mitiku | 200 | Wosen Yitna | 150 |
| Zelalem Mengistu | 307 | Temesgen Tesfu | 200 | Bishaw Kebede(UK) | 100 |
| Anteneh Merid | 300 | Gillian Anderson | 150 | Yohannes Admasu | 71 |
| Sileshi Gelaneh | 300 | MWO Jerry Ohara | 150 | Liz Proszek | 70 |
| Ewnetu Beyene | 240 | MWO Michael Mihalus | 150 | Anne Dunn | 50 |
| Aster Gebreab | 220 | Mary Sawden | 150 | Sharon Goodrige-Simon | 40 |
| Dr. Efrem Alemayehu | 200 | Wilma Jakus | 150 | Tracy Wong | 40 |
| Dr. Yidersal Melese | 200 | Dr. Haile Fenta | 150 | Eyerusalem Ayehu | 40 |

*Jocelyn Green is the board member of DevXchange International, and her commendable contribution to the LIFE scholarship transcends to include her son Russel Green.

**Dr. Jennifer Cosidine & Dr. Melaku G.Desta have been supporting the Scholarship program since the inception of the project.

**For 2009/2010** academic year LIFE Scholarship has continued fund raising activity. So far, LIFE Scholarship has received the donations from the following individuals and organizations (in Cdn$).

Moleche Monnex Insurance on behalf of Yihun A. Belay for his contribution to the LIFE Scholarship project Community Service $500 and Moleche Monex employees contribution collected by Yihun A. Belay $562, totaling $1062

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| Dr. Jennifer Considine | 300 | Dr. Melaku G. Desta | 200 | Aster Gebreab | 130 |
| Scott Dombroski | 50 | | | | |

In addition to a continued participation in the scholarship project, GDA – Canada together with DevXchange international is embarked on School book project to send high-school and college/University text books to Gojjam. Anteneh Merid is shouldering the leadership

responsibility for this daunting task of collecting, organizing, packing, and other logistic responsibility. Anteneh devoted his entire garage for this purpose. More than six thousand text books for colleges and high-schools have been collected and if things go smoothly as planned, the books will be shipped to Gojjam in the summer.

We would like to thank schools that donated books and individuals who contributed their time, money and effort in the book collection process.

In particular we would like to thank Beth Fellows the executive director of Devxchange international for her continued support for this project and teacher Brandi Bailey, Tara Bailey, Amy Reesor, Jennifer Behan, Graham Rayner, Laura, Mary, Angela Spong, Tara Heittola, Teale Heittola, Bruce & Carole Wills, Mekonnen Gebeyehu, Melake Tizazu (who is also collecting books for the same cause). Your support has been invaluable for this noble project.

As noted last year, LIFE Scholarship project is a member of DevXchange International whose mission is “Improving the Lives of people in developing countries by connecting people that care with projects that work”.

Tessema Bitew is now a board member of DevXchange International.

If you want to learn more about DevXchange International, visit www.devxchange.org

In April 2009, Bob Black, the board member of the Devxchange International, traveled to Ethiopia for a working visit and had a chance to meet the GDA(Gojjam Development Association – our implementing partner at home) board members in Addis Ababa. He was briefed by the GDA executive team about various projects GDA is running. He is impressed by the GDA leadership professionalism, and commitment for development projects. Mr. Black has a number of projects in Gojjam region including Moringa tree planting in Gumuz area (multi purpose, edible and nutritious tree), Vocational training for peoples living with HIV, and others.



Mr. Mekonen, Mr. Tessema, and Mr. Anteneh preparing books for shipment to Ethiopia

Finally we would like to thank Yihun A. Belay who stood out as top fund raiser in this year. Yihun has managed to collect more than one thousand dollar from his company and office for our scholarship project.




Ato Tessema Bitew with Board members of DevXange

We would also want to thank the resilient GDA-Canada board members, Temesgen, Zelalem and Yohannes who never give up even when the journey gets difficult.

On a sad note, GDA Canada is saddened by untimely death of an important member Zinash Berhe. Zinash passed away on April 18, 2009 after courageous fight against cancer. Zinash was an exemplary member of GDA Canada. Her contribution for the re-establishment of GDA Canada will remain in the memory of all members who attended the first and second general meeting. May God rest her soul in peace. Zinash survived by her three children, Aelaf, Ahadu, Mahlet and her husband Andsew Beyene.

ድጋፍዎን፣ ምክርዎን፣ አስተያየትዎንና ጥያቄዎን

በዚህ አድራሻ እንጠብቃለን

Gojjam BetreSidiq Scholarship
5268 Cozy Glen Lane
Alexandria, VA 22312
703-980-6650
Gojjam.Scholarship@gmail.com

ባለፉት ዓመታት ያቀረብናቸውን ዘጋባዎች ለማይት ይህን ድህረ-ገጽ የመልከቱ

http://goshana.org/My_Homepage_Files/Page2.html

እናመሰድናለን

ጎጃም በትረጽድቅ ስኮላርሺፕ

# በ2001 የትምህርት ዘመን የበትረጽድቅ ስኮላርሺፕ አሸናፊዎች

## ከምሥራቅ ጎጃም መሰናዶ ትምህርት ቤቶች

| | | |
|---|---|---|
| ደብረ ማርቆስ | ሰናይት ሞላ እጅጉ<br>ሰለሞን ቀለሙ ለይኩን<br>አለሙ መኮንን<br>ይመስገን ይበልጣል |  |
| | እሱባለውዋይቸህ<br>ስጦታው መንግስቴ ማተቡ<br>መላኩ ደግፍ ሁነኛው<br>ውብሊቀር |  |
| ግንቦት 20 | ይልቃልላደመ በላይ<br>ሰናይት ዋለልኘኛንዱዓለም<br>ስሜነህ ደሴ |  |
| ጎጃም በር | ታሪኩ በዛ<br>ነጻነት ተመስገን<br>ማናህሎሽ ሞላ ምትኩ |  |
| የጁቤ | በላይነህ መንግሥቴ በየነ<br>የዝና አያል መኮነን<br>ፈቃዱ ህብስቱ ቢተው |  |
| ደብረወርቅ | አሳየ ገዳሙ ትምራት<br>በጎላውዋጥናፍ መንግስት<br>አዳነች በለቸው ቸኮል |  |

# ከአዊ ዞን መሰናዶ ትምህርት ቤቶች

| | | |
|---|---|---|
| ቲሊሊ | ጌትነት ብርሃን<br>ሰናይት ቢሰነብት ተፈራ<br>አስራት በሪሁን |    |
| አገከሻ | ምንባለ ቢረሳው ጀምበሬ<br>አበበ መንግስት ወልዴ<br>አባይነ የኔ አባት ገረመው<br>ጸሐይነሽ የኔው መለሰ |     |
| ቻግኒ | ዘሪሁን ክንዴ ታደሰ<br>ስንታዬሁ ታደሰ ወርቁ<br>እናትፈንታ ሰውመሆንነንዳለው |    |
| ዳንግላ | ደሳለው ጌታሁንናያሌው<br>ሙላቱ ልየው ንጉሴ<br>አዝመራው ብርሃን ደምሰው<br>የሽማረግ ሽታ መከተ |     |
| እንጅባራ | ገረነው ክንዴ ወርቄ<br>ግዛቸው ታደሰ አየነው<br>ማስተዋል ሃይለማርያም አለሙ |    |

